ነፍሴ በእጁ በሆነችው ጌታ እምላለሁ! እርሷ (ቁል ሁወሏሁ አሐድ) የቁርአንን ሲሶ ትስተካከላለች።" አሉ።

ከአቡ ሰዒድ አልኹድሪይ ረዲየሏሁ ዐንሁ - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: «አንድ ሰውዬ የሆነ ሰው {ቁል ሁወሏሁ አሐድ}ን እየደጋገመ ሲያነብ ሰማ። የነጋም ጊዜ ወደ አላህ መልክተኛ ሶለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም -የአላህ ሶላትና ሰላም
በእርሳቸው ላይ ይስፈንና- በመምጣት ነገሩን በሚያቃልል ሁኔታ ይህንን አወሳላቸው። የአላህም መልክተኛ ሶለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም -
የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና- "ነፍሴ በእጁ በሆነችው ጌታ እምላለሁ! እርሷ (ቁል ሁወሏሁ አሐድ) የቁርአንን ሲሶ ትስተካከላለች።" አሉ።»
[ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪ ዘግበውታል።]

አቡ ሰዒድ አልኹድሪይ ረዺየሏሁ ዐንሁ - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንዳወሱት: አንድ ሰውዬ ሌላ ሰው የ{ቁል ሁወሏሁ አሐድ}ን ምዕራፍ ሲያነብ ሰማ። ምሽቱን ሁሉ ሌላ ምዕራፍ ሳይጨምር እርሷን ብቻ ነበር እየደጋገመ የሚያነበው። የነጋም ጊዜ ወደ አላህ መልክተኛ ሶለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም -የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና- በመምጣት ይህንን አወሳላቸው። የጠያቂው አነጋገርም ምዕራፏን ያሳነሳት ይመስላል። ነቢዩም ሶለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም -የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና- አፅንዖት ለመስጠት በመማል "ነፍሴ በእጁ በሆነችው ጌታ እምላለሁ! እርሷ የቁርአንን ሲሶ ትስተካከላለች።" አሉ።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/65261